ዑነትና ንጋት እያደረ ይጠራል ____ ክፍል ሁለት

በዘመንፍስ ቢያድግልኝ

በክፍል አንድ ከህዋሃት ዲሞክራሲ መጋረጃ ጀርባ የመሪ ተዋንያን ማንነት ለማየትና በጨረፍታ ለማሳየት በግርድፉ ነካክቸው አሎሁ። እንደዑነቱ ከሆነ ለመንደርደርያ እንጂ እጅግ ዘግናኝ የሆኑ ግፍና በደል በትግልና በፍትህ ስም በነዚህ የበግ ለምድ የለበሱ ተዋንያን ተፈጽመዋል።ለመሆኑ ይህን ያቄመ ጸያፍ ተግባር ሲከውኑ ምን ያደርጉ ነበር ብንል ማንነታቸውን ፍንትው አርጎ ያሳየናል _______

አቦይ ስብሃት ከጀርባ ካልሆነ ፊት ለፊት መጋፍጥ አይሆንለትም በተማሪነት ጊዜ እንኳ ትልቁ ዘዴው የክፍል አለቆችን (ሞኒተሮችን) ስብስቦ ተማሪውን እንድያሳደሙ ያደርግ ነበር እንጂ ፈጽሞ ፊት ለፊት ወጥቶ መናገር ዳገቱ ነው። በ1950 ዎቹ መጨረሻ የራስ መንገሻ ሥዩምን አስተዳደር ለማናጋት ያልፈንቀለው ዲንጋይ አልነበረም። ያቺን የራስ ሥዩም አባትነት አቶ ነጋ መነገፋቸው የእግር ውስጥ እሳት ሆናባት አድጋለች። እዚህ ላይ በዛ ዘመን ገና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዕንቅስቃሴ ዕንጭጭ የነበረ ቢሆንም ለድብቅ አላማው መጠቀሚያ ለማድረግ ያልቆፈረው ጉድጋድ አልነበረም።

በወቅቱ የአጼ ዮሃንስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር የነበሩ ለትምህርት ቤቱ በተመድበ በጀት ከክፍለሃገሩ ትምህርት ቤቶች ሥራ አስከያጅ አለመግባብት ሲፈጠር አቦይ ሥራ አስካያጁን በመደገፍ ተማሪውን የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ትግሬ ከቁሙጣ መቼ ወጥቶ ያቃል በሎ ስድቦናል በማለት በተለመደው ዜድ የክፍል አለቆችን በማሳደምና በማግስቱ የትምህርት ቤቱን ደወል በመስረቅ ዛሬ አብርሃ ካስትል( ያኔ በመፈራረስ የነበረ) ደውሉን ውስደው እዛው እይደወሉና እያስደወሉ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ሳይሆን ወደ ዛው እንዲያመራ በማድረግ አመጽ አንድ አስጀመረ።

ውሸት ሽፍጥ ምንም በማር ቢለወሱ ማርነታቸው ሲይሟሽ ዕርቃን ያስቀራሉ; ጊዜና ህዝብ ይታዘባሉ፤ ብለውም ይዳኛሉ፤ ማንም ይሁን ማንም ከጊዜ ዳኝነት አያምልጥም፤ በአሁኑ ጊዜ በወያኔ መንደር የሚስማው ኡኡታ ዐይኔ ግንባር ያርገው ከሚለው የአብው አነጋገር ባለፈ ትርጉም የለውም። በይበልጥ ደግሞ አሳዛኙ ጉዳይ የአቦይና የግብረ አቦሩቹ ሴራና ተንኮል ለይቅርታና ለጸጸት የማይመች ኢሰብዓዊ ድርጊት መሆኑ ገሀድ ሆኖ እያለ ለመሽፈን የሚደረግ ሩጫና የህዝብ ጥያቄና ብሶት አስመስሎ ለማቅረብ መፍጨርጨሩ ነው።

ስብሃት ነጋ ከልጅነቱ ጀምሮ የንጉሳዊ ዘረ ሐርግ መነፈጉ፤ በአድዋ መካንንትና በሌሎች አውራጃዎች የነበረው ፈጥጫና የኔ በሚላቸው ሰዎች የደረሰው ሽንፈት በማንነቱ የፈጠረው የስበዕና ቀውስ አብሮ አደግ ጋደኛው አድረጎ ለበቀል ከሆነለት በድል አድራጊነት ወጥቶ ያጣውን ሹመትና ማዕርግ ለማግኘት አርገዞ የኖረ ግለ ሰብ ነው። ያልተረዳው ግን በቀል ጊዛዊ ዕርካታ ቢያስገኝም የማያቋርጥ ቀውስ እንደሚከት ነው።

"We often believe that exacting revenge is a form of emotional release and that getting retribution will help us feel better. Movies often portray the act of revenge as a way of gaining closure after a wrong. But in fact, revenge has the opposite effect. Even though the first few moments feel rewarding in the brain, psychological scientists have found that instead of quenching hostility, revenge prolongs the unpleasantness of the original offense. Instead of delivering justice, revenge often creates only a cycle of retaliation." Democratic underground.com website

“ብዙ ጊዜ በቃኝ የማይል የበቀል ድርጊት የሀቡዕ ስሜታው ፍላጎት ሲሆን በቀል ይተናጋው ስሜታችን የሚያረጋጋ መስሎ ይታየናል። ሲናማዎች ብዙውን ጊዜ የበቀል ዕርምጃ ለተፈጸመ የስህተት ዕርምጃ መድምደምያ አርገው ያሳዩናል፤ ጉዳዩ ግን የተቃራኒው ነው። ምነም እንኳን ለጊዜው ዕርካታ የተሰማን ቢምስልም የሥነ አእምሮ ሳይንቲስቶች የደረስቡት የምርምር ጥናት የሚመለከተው በደልን ከምደምደም ቀደም ብሎ የደረሰውን የስቆቃ ስሜት ይበልጥ ያራዝመዋል። ፍትህን ከማምጣት በቀል የማያቋርጥ አዙሪት ወስጥ ይከታል።” ዲሞክራቲክ አንድር ግራውንድ ዶት ኮም ድኅረ ገጸ

አንድ የስብሃት ቤተስብ የቅርብ ጋደኛ እንዲህ ሲሉ አጫወተውኛል። ሉዑል ራስ ሥዩም መንገሻ በ1953 የጀነራል መንግስቱ ንዋይ የመፈንቅል መንግሥት ሙከራ ከሞቱ በኃላ ልጃቸው ሉዑል ራስ መንገሻ ሥዩም በቦታው ተትከተው ትግራይን ማስተዳደር ይጀመራሉ።

ከዓመታት በኃላ ሥበሃት ወደ ራስ መንገሻ በመሄድ እንዲህ አላቸው “የወረዳ አስተዳደርነት ይስጡኝ ብሎ ይጠይቃቸዋል።” እሳቸውም ሁሉም ወረዳዎች ተይዘዋል፤ ባይያዙም ዋናው እንኳ ቢሞት ምክትሉ እዛው ይጠብቃል ማንን አንስቼ ነው የምሾምህ አልችልም ሲሉ መለሱለት” እኚሁ የቤተሰቡ ጋደኛም አያይዘው እንዲህ አሉኝ “ስብሃት ይህን ጥያቄ ያቀረበው እኔም የራስ ሥዩም ዘር እኮ ነኝ ከሚል ውስጡ የሚያብሰለስለው ጉዳይ” ሲሆን አሉ “ እሺ በለው ከስጡት አሃ ዘርነቴ ተቀብለወኛል በሎ ለመጽናናት አልያም ያንኑ በቤተስቡ ሲብላላ የነበረው ጉዳይ ለማጠናከር የተጠቀመበት ዜዴ ነው።”

“Greed is a bottomless pit which exhausts the person in an endless effort to satisfy the need without ever reaching satisfaction.” - Erich Fromm, *Escape From Freedom*

*“ስስት መጨረሻው እንደ ማይታውቅ ውይም መጨረሻ የለለው ጉድጋድ ነው። ስስት የተጠናወተው ሰው መጨረሻ የለለው ፍላጎት ገበቶ ምንም ሳይረካ መና ይቀራል። ኤሪክ ፍሮም _ እስኪፒ ፍሮም ፍሪደም*

*ስብሃት በውስጡ ያመቀው የዘር ሐረግና የሥልጣን ጥማት መጨረሻ በሌለው ፍላጎትና ምኞት ተጠምቶ እጁን ሊወጣው በማይችል የደምና የታሪክ በደል ተነከሯል፤ በመሆኑም ሕይወቱ እስካለ መጨረሻ በሌለው ጉድጋድ መገባቱ እንካ ቢረዳም ያየተመኘው ነገር እስካላገኘ/ኢያገኝም/ ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስስ ኢይለቅም እዲሉ ሰውን ከማሳሳት ገብረ አብር ከማድረግ ወደኃላ እንደማይል በግልጽ እይታየ ነው።*

*አቦይ ህውሃት የተቀላቀልኩት በተቋቋመ በውሩ ነው ቢልም የቀድሞው የሲዳሞ ከፍለ ሀገር ትምህርት ቤቶች ሰነድ የሚያሳየው ግን እስከ ግንቦት 30/1969 ድረስ ደመውዝ ፈርሞ መውሰዱ ሲሆን ቀደም ሲልም በዛው ዓመት የፋሲካ በዓል በከምባታና ሀድያ ሆስዕና ከተማ አብራቸው ማክበሩ በቅርብ የሚያውቁት ይናገራሉ፤ ይህን የጠቃቀስኩት ደብቅ ዓላማው ለመፈጽም ይጠቅማል የሚለው ከማለትና ከማድረግ ወደኃላ እንደማይል ለማሳየት ሲሆን ይህ ያስባለው ከመስራቾቹ አንዱ ነኝ ለማለት እንደሆነም ለማሳየት ነው።*

*መቼም ይሁን መቼም ይቀላቀል የመጀመርያ ጉብዔ በለው በጠሩት ስብሰባ በመለስ ፊተውራሪነት እየተረዳ የድርጅቱን ቁንጮ ሥልጣን ጨብጠ። ይህም የፈለገውን ለማድረግ ተጨማሪ አቅም ሰጠው። ይሁንና መጀመርያውም የመለስ ቡድን ጉባዔው ሲጠራ እንዲሳትፉ የተደርጉት በጥንቃቄ ተመርጠው የኛ የሚልዋቸው ስለነበሩ በወቅቱ ድርጅቱን ለመምራት ብቃት የለውም ያሉ ሁሉ ጥርሱ ውስጥ ገቡ በዚህም፤*

1) *አክሮና በበቂ መረጃ በግንባር ቀደም የተከራከረውና በብቃትም በትምህርትም የሚበልጠውን ራስ ወርቅ ቀጸላን ዒላማ በማድረግ እንደ የሕንድዋ ኢንድራ ጋንዲ  በአጃቢ ተብየ በጀርባ እንዲመታ በማደረግ  አሰውገደው። የሺሬው አርበኛና በቀዳማዊ ኃይልሥላሴ ፓርላማ የሺሬ ተውካይ የነበረውና*

*በሺሬ በረሀዎች ህዋሃት ተቀባይነት እንዲያገኝ ከፍተኛ ሚና የተጫወተው ገሠሠ አየለን፤ የእንደርታው ዘርኡ ገሠሠን በረቀቀ ዜዴ አስወገደ፤*

2) *በ1950 ዎቹ በአጼ ዮሃንስ ትምህርት ቤት ሃሳቡን ይቃወሙ የነበሩ አሊያም ይበልጡኛል የኋላ ኋላም የያዘውን ሥልጣንና ደብቅ ዓላማ ያደናቅፉብኛል የሚላቸውን በረቀቀ ዜዴ መመንጠር ጀመረ፤ በዚህም ለዘበተኛ የሚላቸውና አባቶቻቸው ኢትዮጵያውነት ያንጸባርቁ ነበር በሎ ያሰባቸው ከአዲ አቡን ውጭ ያሉ የኢድዋ ልጆችን ጨምሮ አሁንም መልቀም ቀጠለ። በዚህ ዕርምጃው ከተወገዱ ውስጥ አበራ ማንክያ፤ዓለምሰገድ ገብሩ፤ ገብረሕይወት ውልደገብሬኤል ይገኙበታል።*

3) *አስገራሚው ግን ህንደያ አበራ የሚባል የ1950 ዎቹ የትምህርት ቤት ኣቻውና በትግሉ በህዝብ ማደራጀት ይሰራ የነበረ ደንገት በመንግሥት ኃይሎች ሲያዝ አይ እጄ ልስጥ ነው የመጣሁት ስላላቸው መርጃ ለማገኘት ሲባል በዙ አስቸጋሪ ባልሆነ ኢያያዝ ይዘውት ስለነበርና በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ ጋደኞቹ ሊያስመለጡት እንድሆነ በገብሩ አሥራት በኩል ስብሃት ሲስማ ከብሪት እያሉ የሚጠርዋቸው ተወረውሪ ውይም ስላይ ጦር በመላክ አለበት የተባለው ሥፍራ ላይ ቶክስ በማስከፈት የመንግሥት ካድሬዎች ውሸትህ ነው በማለት ለበቀል አውጥተው እዲገድሉት ያሴርው ሴራ ነው።*

4) *ምንም እንኳ በአንደኛ ጉባዔ ተብየው እነ አርጋዊ በርሔ ከስልጣን ቢወርዱም በአካባቢው መኖራቸው አልተመቸውም፤ እንድሌሎቹ እንዳያስውገዳቸው ቀደም በለው በአመራር በነበሩበት ደጋፊ አፍርተዋልና ኢያውጣም፤ ስለሆነም አሁንም በመለስ፤ በዓባይና በሥዩም መስፍን የሚመራው ቡድን አቀናባሪነት የርዕዮተ ዓለም ክርክር በመከፈት እዲብጠለጠሉ አመቻቸ፤ ይህንንም በቪድዮ እንዲቀርጽ ተደርጎ በየቦታው ላሉ ታጋዮች እንዲስራጭ ተድረገ። እነ አረጋዊ በርሔ እስከዛሬ በሁለቱም ወገን ባልተገለለጸ መንገድ ህይወታቸው ይዘው ያልተረጋገጠ ቢሆንም ተደጉመው ለስደት ተዳረጉ። ይህም ቪድዮ ህዋሃት ሥልጣን ሲይዝ የመለስን ስብዕና (personality cult) ለመገንባት በትግሉ ወስጥ ላልነበሩ ደጋፊ ተብየ ለዓመታት እንደመቀስቀሻ ተጠቅመውበታል።*

5) *መለስ፣ ዓባይና መስፍን ለምን ተጠቀም ቢባል የራሱ ምክንያት ቢኖረውም እነሱም የየራሳቸው ምክንያት ነበራቸው። መለስ እሱም ከትምህርት ቤት ጀምሮ የሥልጣን ጥም አለበት፣ የዊንጌት ተማሪ በነበረበት ጊዜ የክፍል ጋድኞቹ አንተ በሎ ለገስ ሲሉና ሲቀልዱበት ቆይ እነግሳሎህ ብሎ ይመልስ እንደነበረ ይናገራሉ ይህም የሥልጣን ጥሙ ገና ከልጅነቱ እንድነበረ ሲያሳይ ስብሃትን መደገፉ በስተጀርባ የራሱን ዕቅድ ለማመቻቸት መሆኑ ገልጽ ነው የሆነውም ይህው ነው። ሥዩም መስፍንም ግበረስጋ በሞት በሚያስቀጣ ጊዜ ሱዳን በነበረው ጽህፈት ቤታቸው ትሰራ ከነበረች ታጋይ ልጅ ስለውለድና ይህን ሚስጥረ እንዳታወጣ በሴትዋም በዙ አላስፈላጊ ነገሮች ስለፈጸመ አቦይ ይህችን ቀይ ካርድ ይመዝበታል። ዓባይ/ትክክለኛ ስሙ አምሃ/ አድር በዬ ዋንዛዬ ነው የኃይል ሚዛኑ ወደ አደላ ዘው የሚል እንገዴ ልጅ ነው። ይህም በህዋሃት በተፈጠረው መስነጣጠቅ የታየ ነው።*

6) *አቦይ ሌላው ዜዴው በማዕከላዊ ኮሚቴ ይተካተቱትን አባላት በተናጥል የማስር ብሎም እስከ ሞት ድረስ የመፈረድ ሥልጣን እንዲኖራቸው ማድረግና የውንጀሉ ተባባሪ እንዲሆኑ መግፋፋት ነው።*

7) *በዚህ ውስብስብ የበቀል ፖለቲካና በተፈጠረው የፍርሀት ደባብ ብዙዎች የትውልድ መንደራቸው አዲ አቡን አሊያም ኣድዋ ማለት ጀመሩ። አስቂኝና አሳፋሪው ደግሞ ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ በአጼው ጊዜየ የነበረ ጋዜጠኛ መርስዔ ሀዘን አበበ የዛሬዎቹ ባለ ጊዜዎች ቼቸንያ ተብሎ በተሰየመው የባለ ጊዜነት መታያ የምሽት መዘናኛ ሁሉ በእፄው ጊዜ ንፋስ ስልክ አካባቢ ነብር፤ ታድያ መሳፍንቱና መካንንቱ ዘና የሚሉበት ቦት ይታዘብና “ማታ ማታ ስኮትላንድ ጥዋት ጥዋት ላም በረት” በሚል ርዕስ ጎንተለ የሚደርግ ጽሁፍ አዲስ ዘመን ላይ ያወጣል። በዚህ ተድፈርን ያሉ የዚያን ዘመን ባለ ጊዜዎች የማስታወቅያ ሚኒስትሩን እንዴት እንዲህ ይደርጋል በለው ወተወትዋቸው፤ እሳቸውም ጋዜጠኛውን ጠርተው ከውቀሱና ከተቆጡ በኋላ በደመወዙ እንድሚቀጡት ነገርወት የሚኒስትሩ የአስተዳድር ሀላፍ ያስጠራሉ፤ በመኃሉ ለመሆኑ ከየት ከፍለ ሃገር ነህ ይሉታል፤ ብልጡ ጋዜጠኛ ጌታየ በሚስቴ በኩል ጎጃሜ ነኝ ይላቸዋል (ጎጃሜ መሆናቸው ያውቃልና)፤ ቀና ይሉና ወርበላ በል ውጣ ሲሉ ሳይቀጡ*

*ያስናቡቱታል። ታድያ ከዓመታት በኃላም ይህን ነገር ተድገመና በአቦይ ዘመንም በሚስቴ በኩል አዲ አቡን ነኝ ኢድዋ ነኝ ባዩ ስፍር ቁጥር የለውም። መላ ታጋይና፤የትግራይ በተለይ የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ የሚያቀው ሀቅ ስለሆነ ጸሀፊው ስዎችን በስም መጥቀስ አላስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።*

*ከዚህ ሁሉ ቅንበርና ውጣ ወረድ ህዋሃት በውደም በግድም የትግራይ ወጣቶችን በመማገድ ትግሉ ቀጥሎ አቦይ መሉ በሙሉ ድርጅቱን የግል ንብረት በሚመስል መልኩ ተቆጣጠርው። መለስም የፖለቲካ ትምህርት ቤት በሚል ሃላፊ ሆኖ የራሱን አድር ባይና እንዳሻው የሚያሽከረክረው የካድሬዎች ሠራዊት መገንባት ጀመረ። በዚህም ትግሎ እየገፋ በለስ እይቀና ሲሄድ መለስ በቂ የራሴ የሚለው ኃይል አበጀ። ኢይደርስ የለምና ያቺ ይመኖት የነበረች ቀን ደረሰች።*

*ህዋሃት በመላ ኢትዮጵያ ኢፒኤልፍ በኤርትራ በለስ እየቀናቸው ሲሄድ በውቅቱ ኢትዮጵያን ያስተዳድር ከነበረው ወታድራዊ መንግሥት ለድርድር እንዲቀመጡ የዓለም የፖለቲካ ተዋንያን ጥሪ አቀረቡ ሁለቱ ወገኖች ሲስማሙ እንኳንና ለትግራይ ሕዝብ ለታጋዩ ግልጽ ባልሆነ መንገድ መለስ ብቅ በማለት ወደ ሎንድን ለድርድር ተጓዘ። በትረ ሥልጣኑም ተርከበ።አቦይ የኔ በሎ የተኮፈሰለት ድርጅትና ሥልጣን ተቀናቃኝ ተውለደበት።*

*አቦይም ከመጋረጃ በስተጀርባ በአልሞት ባይ ተጋዳይ ቀጠለ። ሁለቱም የቋመጡለትን ሥልጣን በጎሪጥ እይተያዩና አንዳንዴም እይተቻቻሉ ወስጥ ለውስጥ እይተዶላለቱ ቀጠሉ። ለዚህም ህዋሃት የውስጥ ችግር በገጠመው ጊዜ አቦይና መዋቹ ክንፈ( የድህንነት ሀላፊ የነበረው) ከነስዬ ጀርባ እንደነበሩና የኃይል ሚዛኑ ወደ መለስ ሲያዘነብል ሸረተት እንዳሉ ውስጥ አወቂዎች ሹክ ብለውኝል። ይህም ተስፋየ ወልድስላሴ የደርግ ድህንነት ሃላፊ በግንቦት 8/1983 በደርግ ላይ በተሞከረው መፈንቅለ መንገሥት ዓይነት ነው ተብሎለታል።ያም ሆነ ይህ ማርክ ትዊን እንዳለው ራስህን በቡዛኃኑ ጎራ ስታገኝ ራስህን ማስተካከል/መለውጥ አለብህ መርህ የህዋሃት ሹማምንት ኢትዮጵያዊ ዜማ ማዜም ጀመሩ ከልብ ይሁን ከከንፈር ______________።*

“Whenever you find yourself on the side of the majority, it is time to reform (or pause and reflect).”
**— Mark Twain**

**“ራስህን ከብዙኃኑ ጎራ ጎን ስታገኘው ራስህን መለውጥ/ ማስተሾመካከል ይኖርብኃል” ማርክ ቲዊን**

*ነገር ግን በ1968 ባውጡት ማኒፈስቶ ያሰፈርዋት “የመጨረሻው የቲፒኤልፍ ግብ የትግራይ ህዝብና መሬት ነጻ በማዋጣትና ከኢትዮጵያ በመገነጠል የታላቅዋ ትግራይ ሪፓብሊክ ማቋቋም ነው” የምትለዋ ግን በኢትዮጵያዊነት ዜማው አልተዋሀደችም ይልቁንስ በህገ መንገሥት ስም ባአንቀጽ 39 በልዩ ዜዴ እስከ መገንጠል በሚል ተካተተች ፤ የውስጥ ሴራውን ምንነት ያልተረዱም ጨፈሩ።*

“C) The final goal of the TPLF is to secede from Ethiopia as an independent “Republic of Greater Tigray” by liberating the lands and peoples of Tigray”

*እዚህ ላይ ጽሀፊው እውን ህዋሃት የትግራይ ህዝብ ብሎም የኢትዮጵያ ድርጅት ነው የሚል ጥያቄ ለማንሳት ይገደዳል። ለምን ቢባልም ___________________ እንሆ*

1) አቦይ የሥልጣን መንበሩ እንድያዘ ምንም እንኳ ወስጥ ለውስጥ በህዋሃት የሚውጠነጠን ሴራ በዚሁ ረገድ የነበረ ቢሆንም የመጀመርያው አጀንዳው የኤሪትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብሎ ታጋዩን እንዲያምን ማድረግ ውይም ማስገደድ ነበር። ለዚህም ትግራይ ወስጥ ጳዊ በሚባል በረሃ ታጋዮች ስብስቦ የአካባቢው የህዝብ አድራጅ የሆነውን ስው ጋር በመሆን ይህንኑ አጀንዳ ለማስረጽ ሀ በሎ ጀመረ። ይሁንና በሱና በአድራጁ  መድርክ ላይ አለመግባባት በመፈጠሩ ታጋዩ ምንደነው ውይይቱ የግላቹህ አድረጋችሁት ብሎ ይጮኃል፤ በዚህ ጊዜ አደራጁ አይ ስብሃት የኤሪትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ኢሕአፓ አይደለም በሎ አሸፈርኚ ስለአለ ልንመታው ነው እያለ ነው በሎ ይመልሳል፤ በዚህም ታጋዩ ባንድ ድምጽ የኤሪትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም ኢሕአፓም ነጻ ድርጅት ስለሆነ መመታት የለበትም መወያየት አለብን እንጂ ሲል ታጋዩ ይመልሳል፤ አቦይም በድንጋጤ መድርኩን ለቆ ቀጣይ ሴራውን እያብስልሰለ ይውጣል።
2) ከዚህ ቀደም ሲል ግን አቦይ ዘጠና አምስት በመቶ የህውሀትን ማዕከላዊ ኮሚቴና ሥራ አስፈጻሚ በአዲ አቡን ልጆች አብዛኞቹ የኤሪትራ ትወልድ ያላቸው አልያም ሙሉ ኤሪትራውያን ሆነው ትግራይ ተውልደው ያደጉ አካተተ በዚህም የኤሪትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው የሚል አቋም አስውስኖ ታጋዩ ይህንኑ እዲፈጽም መመርያ አስተላለፈ።
3) ይህን ውሳኔ ያልተቀበሉ ለዘብተኛ ለትግል ያልመጡ በማለት መነጥል ጀመረ። በርከት ያሉ ታጋዮች ከተጠመደላቸው ፈንጂ እያመለጡ ትግሉን ጥለው ወደ ስድት ለመሄድ ተገደዱ።
4) አቦይ ያቀደውን በቀሩት ታጋዮች ብዙም የዚህን ወስብስብ ሴራ ያልገባቸው በትምህርትም እምብዛም ያልሆኑትን የትግራይ አርሶ አድር ልጆች ይዞ ኢትዮጵያዊ ይዘት ያላቸውን እነ ኢድዩን፣ ኢሕአፓን ለማጥፋት ዘመተ።
5) ከዚያም ጀብሃ( ሌላው የኤሪትራ ነጻ አውጭ ብሎ ይታገል የነበረ) ለማጥፋት ተነሳ። ለዚህም አንድኛ ጀብሃ ቲኤልኤፍ የተባለ ሌላ የትግራይ ነጻ አውጪ ይደግፍና ይደገፍ ስለነበረ፤ ሁለተኛ እነ አቦይን የሚደገፈውና ያስለጠነውን ኢፒኤልፍን ስለሚቃወምና የትግራይ ሪፐብሊክ (ትግርኛ ተናጋሪ ሁሉ የሚያቅፍ) ሃሳብ በጥርጣሬ ስለተመለከተ ብቻ ሳይሆን ኢፒኤላኤፍን መድገፍ ለትግራይ ሪፐብሊክ ዓላማ ያመቻል በሚል የተሸረበ ነው። ለዚህም ዓላማ አረጋዊ በርሄና ገብሩ አስራት በደቡብ ምዕራብ ያለው ሠራዊት እንዲይስተባብሩ ወደ ሳምሬ በ1971 ያሰማራል ግን ሠራዊቱ ሳይቀበላቸው ቀረ።

የበረሀው ሴራ ይህን ሲመስል የጊዜ ጉዳይ ወደነሱ አድለቶ መላ ኢትዮጵያን ከመሰለሎቻቸው ሲቆጣጠሩ አዲስ ተንኮልና ሴራ ቀጠሉ።

1) ምንም ዓይነት የህዝብ ይሁንታ ሳያገኙ በጥድፍያ የኤሪትራ ሪፈረንደም ማካሄድ ጭራሹኑ ትግረኛ ተናጋሪ ሁሉ ውጣና ደምጽ ስጥ እያሉ በቀበሌ አስተዳድር በመቀስቀስና በማዘዝ ሲያኮናውኑ ወዲውኑ ዕውቅና በመስጠትና  ዓለም ዕውቅና እንዲይስጥ ተሯሯጡ።
2) ፌደራሊዝም ስም ህገሪቱን መሰንጣጠቅ። ይህም ሕገ መንግስት ከማርቀቅ ይጀመራል። ይሁንና ቀደም ሲል ባወጡት የቲፒኤልፍ ማንፌስቶ መሠረት ማዋቀር ነው፤ ማኒፌስተውም እንዲህ ይላል”

ሀ) “ ባለንበት ዘመን የነበረውን የብሔሮች ቅራኔ እየተባባሰ በመሄዱ እነዚህ ብሔሮች ተባብረው ባንድነት እንዲታገሉ ማድረግ በጣም አስቸጋሪና የማይቻል ሆኖ ይገኛል። ይህ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ስሜት (በተለይ በብሔረ-ትግራት) የመደብን ንቃት ሸፍኖት ይገኛል። ይህም ሊሆን የቻለው ጨቋኝና ተጨቋኝ ብሔሮች ለብዙ ዘመናት በሃይል ተባብረው እንዲኖሩ በመደረጋቸው የተጨቆኑት ብሔሮች ጭቆናውን ሊሸከሙት አልቻሉም፤” የቲፒኤልፍ የ1968 ማኒፌስቶ

3) ይህው ዕቅድም ተግባራዊ ለማድረግ የብሄር ቤሄረ ስብ መብት የሚል ዜማ በማቀንቀን በውስጥ ግን የሞግዚት አስተዳድር ዘረጉ የቲፐኤልፍ የማዕከላዊና የሥራ አስፍጻሚ ሰዎች በአማካሪ ስም ተመድቡ

4) የኤሪትራ ነጻነት ሲቀበሉ ራሳቸው ባሉት የኤሪትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው" በሚለው እንካ ብንሄድ የአፍሪካ አንድነት  ባጽደቀው ቻርተር (የይትኛውም አባል ሃገር ደንበር ቅኝ ገዥዎች በተውት መሰረት የጽና ይሆናል ይላል") በዚሁ መሰረት ቅኝ ገዥ ያልዋት ኢትዮጵያ ባካለለቸው ድንበር ማካለል ሲገባቸው ጣልያን በነደፈው ካርታ ተደራደሩ። ኢትዮጵያንም ወደብ አልባ ሃገር አርግዋትም።
5) ይህን ጉዳይ የተቃወሙ በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ተሸነፉ በሚል ሽፋን አንድ በረሀው ይመንጠሩ ጀመር። ከነዚህ ኃይሎም አራአያ (ሜጀር ጀነራል) ስሙ በስፊው ይነሳና ተውዳጅነት በህዝቡም በስራዊቱም እያገኘ መጥቶ ነብር። ይሁንንና ፕሮፊሴር እንድርያስ እሺቴ ጋብዞ ወስደው በተባለ ሆቴል በጥይት ተገደለ። የሚገርመው አንድ የኢትዮጵያ ጀነራል በጥይት ተመቶ ለሰዓታት ሳይነስ ደሙ እየፈሰሰ መቆየት ጥያቄ ያስነሳል። ፕሮፌሴር እንድርያስም አንድ ቀን ንስሃ ይገቡና ሃቁን ይነግሩናል እያለ የኢትዮጵያ ህዝብ እየጠበቀ ነው።
6) የድህንነት ሃላፊው ከንፈ ሞትም ጥያቄ እንደጫረ አለ። ምንም እንኳ በመዋችና ገዳይ በብረሃ የነበረ ቅራኔ መኖሩን በቅርብ የሚያውቃቸው ቢናገሩም የግድያው ክንውን ግን ያልተመለሱ ጥያቄዎች እንዳስነሳ ነው። አንድኛ ጀነራል መኮንኖች ሳይቀሩ ምንጥር ተድርገው ተፈትሸው በገቡበት ስብሰባ አንድ ሻለቃ ሽጉጥ እንዴትና በምን ምክንያት ይዞ ገባ፤ ሁለተኛ ከተኮሰ/ከገደለ በኃላ እንዴት የክንፈ ጠባቂዎች ሳይገድሉት ወይም ሳያቆስሉት ቀረ፤ ሦስተኛ የክንፈ ሬሳ ከወደቀበት ሳይነሳ መለስ ከንፈ ቢሮ ለምን ሄደ፤ አራተኛ የክንፈ ምክትል የነበረው ደብረ ጽዮን ብድግ አድርጎ በተራ ካድሬነት ወደ ትግራይ ለምን ተላከ የሚሉ ናቸው። ከንፈ የጎንደር የዘር ሓርግ ስላለው ስብሃትና መለስ ላቀዱት ሴራ ዕንቅፋት ይሆናል ብለው ገና የራሱ የሆነ ኃይል ሳያደራጅ ከውዲሁ ለመቅጨት ታስቦ ይሆናል የሚሉም አልጠፉም። በነገራችን መቀሌ ውስጥ በመለስና በነስዬ ቡድን በተካሄደው ስብሰባ የስዬ ቡድን ስብስባው ረገጦ ሲወጣ በ2 የመጋጋዣ ሂሊኮፕተር ኮማንዶዎችን በተዋጊ ሄሊኮፕተር አሳጅቦ መቀሌ በመሄድ ከስብስባው ይዞት በመውጣት ወደ አዲስ አባባ በመመለስ ከነበረው ውጥረት ያዳነው ክንፈ ነብር።

ህዋህት ይህን የመሰለ የተውሳሰበ የተንኮልና የበቀል ሴራ የተጠመደ ከትግራይ ዓላማና ታሪክ ፈጽሞ የማይገናኝ ተረት ተረት እየተቀኘ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደባ መሰሪ ድርጅት መሆኑ ግልጽ እየሆነ ነው። ጉድጋዱ የተማስ ልጡ የራስ ስብሃት አሁንም ዓይኔን ግንባር ያርገው እያለ የትግራይን ህዝብ ለዳግም እልቂትና ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ለማራራቅ ጎንበስ ቀና እያለ ነው።

መላው የትግራይ ህዝብ በግንባር ቀደም የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ እኛም ነቅትናል __________ እንዲሉና በቃ ሊሉት ይገባል። ኤሪትራውያን የትግራይ ሪፐብሊክ ጉዳይ ስላልጣማቸው ህውሃትን ፊት ነስትዋታል። ቀደም ሲልም ይህን ነገር ያልተዋጠላቸው አቶ ኢሳያስ በሩቁ ሲሉ ቆይተዋል። የትግራይ ህዝብ ከኤሪትራውያን ምነም ችግርም ጠብም የለውም። በተለይ በሃሰት ፕሮፖጋንዳና በጥቅማጥቅም ዓይናቹህ የተጋረደ የትግራይ እንዲሁም ባለፉት 27 ዓምታት በጥቅም የተቆራኛቹህ የተለያይ የብሄረ ስብ ስም ይዛቹህ በውስጣቹህ ግን የህዋሃት አጀንዳ የምታራምዱ ወገናቹህ እይታዘባቹህ ነውና ወድ ህዝባቹ ተመለሱ። በመጨረሻም አንድ የፌስ ቡክ ወዳጂ በላከልኝ መልዕክት ልቋጭላቹሁ።

አንድ አውሮፕላን የሚያጸዳ ግለሰብ የአብራሪውን ክፍል (cockpit) እያጸዳ ድንገት በክፍሉ ውስጥ አንድ መጽሐፍ አገኘ:: የመጽሐፉ ርዕስ "How to fly an aeroplane for the beginners (Volume 1) ይላል:: የመጀመሪያውን ገጽ ገለጠ እንዲህም ይላል:- "የአውሮፕላኑን ሞተር ለማስነሳት ቀዩን መጫኛ (red button) ይጫኑ" ይላል:: አደረገው:: የአውሮፕላኑም ሞተር ተነሳለት:: ተደሰተ:: ቀጠል በማድረግም 2ኛውን ገጽ ገለጠ:: "አውሮፕላኑን ለማንቀሳቀስ ሰማያዊውን መጫኛ (blue button) ይጫኑ" የሚለውን አገኘ:: ተጫነው:: አውሮፕላኑም በሚገርም ፍጥነት መሄድ ጀመረ:: አሁን መብረር ፈለገ:: 3ኛ ገጽ ገለጠ:: "አውሮፕላኑ እንዲበር ለማድረግ እባክዎ አረንጓዴውን መጫኛ (green button) ይጫኑ" የሚል አገኘና ደስ እያለው

ተጫነ:: አውሮፕላኑም በረረ:: ማብረር በመቻሉ በጣም ተደሰተ:: ለ20 ደቂቃዎች ያህል በረረና አሁን ማሳረፍ አለብኝ ብሎ አሰበ:: የመጽሐፉን ገጽ 4 ገለጠ::

ገጽ 4 እንዲህ ይላል:- "አውሮፕላኑን እንዴት እንደሚያሳርፉ ለመማር እባክዎን 2ኛውን መጽሐፍ (Volume 2)

Moral of the lesson
================
እባክዎ ያለሙሉ መረጃ (information) ምንም ነገር አይጀምሩ! ግማሽ ዕውቀት አደገኛ ብቻ ሳይሆን አውዳሚ ነው::

ምንጭ:- Endtime Stories
ትርጉም: NT

የህዋሃት ግንባር ቀደም አመራሮች ፍላጎታቸውን ለሚሟላት የሰው ስቃይና መከራ ደንታ አይሰጣቸውም ዳላይ ለማ ይህን በሚመለከት እንዲህ አሉ

"All suffering is caused by ignorance. People inflict pain on others in the selfish pursuit of their happiness or satisfaction." **Dalai Lama**

"ሁሉም ስቃይና ሰቆቃ የሚከወኑት በድንቁርና ነው። ሰዎች የራሳቸውን ስግብግብ ዓላማ ለሚሟላትና ለራሳቸው ዕርካታ በሰዎች ላይ ስቃይና  መከራን ያድርሳሉ" ዳላይ ለማ